# መመሪያ/ደንብ

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS (MCPS)**
ሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

| | |
|---|---|
| ከዚህ ጋር አግባብ ያላቸው/የሚዛመዱ:- | COB-RA, COB-EA, COC-RA, COC-EA, COE-EA, COE-EB, JFA, JFA-RA, JGA, JGA-RB, JGA-RC |
| ኃላፊው ጽ/ቤት፣- | የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ<br>ዋና የሥራ ሀላፊ |
| የሚዛመዱ ምንጮች | ከጦር መሳሪያ ነፃ ት/ቤቶች ደንብ፣20 ዩናይትድ ስቴትስ ኮድ፣ ቻፕተር 70፣§18-921፤የሜሪላንድ አኖቴትድ ኮድ፣ የወንጀለኛ ሕግ አንቀጽ፣ §4-102፤ የሜሪላንድ ደንቦች ኮድ፣ §13A.08.01.12-1 |

## የጦር መሳሪያዎች

I. ዓላማ:-

በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ የጦር መሣሪያ ከተገኘ መከተል የሚያስፈልገውን ቅደም ተከተል ለመመስረት።

II. የቀድሞ መነሻ

በፌደራል ህግ እንደተገለጸው እና በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ - MCPS Exhibit COE-EB፣ ላይ እንደተደነገገው የሜሪላንድ ህግ ጥይት የሚተኩስ መሣሪያ (ጠመንጃ፣ ሽጉጥ፣ ወ.ዘ.ተ) መሣሪያ (U.S.Code), ጩቤ/ቢላዋ (ስለት ያለው መሣሪያ)፣ እና ማናቸውንም ዓይነት ህይወት የሚያጠፋ/የሚገድል አስጊና አደገኛ መሣሪያዎች በፐብሊክ ስኩል/በህዝብ ት/ቤቶች ንብረት ውስጥ/ላይ መያዝን ይከለክላል። በተጨማሪም፣ የአካባቢ የትምህርት ሥርዓቱ በጣም ጥብቅ እና አስገዳጅ ደንቦችን እና መመሪያዎችን እንዲያዳብሩ የሜሪላንድ ህግ ኃላፊነት ሰጥቷል። በተጨማሪም፣ የሜሪላንድ ሕግ ለአካባቢ ትም /ቤት ስርዓት የበለጠ ጥብቅ ደንቦችን እና ሂደቶችን እንዲያዳብሩ እና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሥልጣን/ኃላፊነት ሰጥቷቸዋል።

III. ትርጉሞች

A. የጦር መሣሪያዎች ትክክለኛ ቅጂ ጠመንጃ/ሽጉጥ የሚመሳሰል፣ የጦር መሣሪያ ተመሣሣይ ተደርገዉ የተሠሩ ማናቸውም ዓይነት ኢንስትሩመንቶች/መሳሪያዎች ናቸዉ።

B. የ ሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ተብሎ የሚገለጸው ማንኛውም ት/ቤት ወይም ሌላ የ MCPS ንብረት/መገልገያ፣MCPS በባለቤትነት የያዘው ወይንም በ MCPS የተያዙ ቦታዎች/ይዞታዎች፣ የ MCPS አውቶቡሶች፣ እና ሌሎች ተሽከርካሪዎች፣ እና መገልገያዎች/ማዕከላት እና/ወይም MCPS ስፖንሰር አድርጎ የተማሪዎች እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱባቸው መሬቶችን ያጠቃልላል።

C. ርእሰ መምህር/ተወካይ እንደአግባቡ ለት /ቤት ወይም ለቢሮ ኃላፊ የሆኑትን አስተዳዳሪን ያመለክታል ።

D. የጦር መሣሪያዎች ተብለው በጅምላ የሚገለጹት በአጠቃላይ በሰውነት ላይ ከባድ ጉዳት የሚያደርሱ፣ እና ማናቸውም እንደ መሣሪያ የሚያገለግሉ ነገሮች፣ ጠመንጃ/ሽጉጥ፣ ወ.ዘ.ተ፣ ጩቤ/ቢላዋዎች፣ ከብረት የተሰሩ ናክልስ/ knuckles፣ ናንቻክስ/nonchakus፣ ቢቢ ገንስ/ BB guns፣ ፔይንትቦል ገንስ/paintball guns፣ እና ፒለት ገንስ/ pellet gunsን የሚያካትት ሲሆን በዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።

## IV. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. ማንኛውም የታወቀ ወይም አንድ ሰው በ MCPS ንብረት ላይ ያልተፈቀደ መሣሪያ ለመያዙ/ለመያዟ በቂ የጥርጣሬ ምክንያት ካለ ወዲያውኑ ለርእሰ መምህር/ለተወካይ ሪፖርት ይደረጋል።

B. ተገቢ ምርመራ ከተደረገ በኋላ፣ ርእሰ መምህር/ተወካይ እንደሁኔታው የሚከተሉትን ታሳቢዎችን የሚያካትት ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ይወስናል/ትወስናለች—

1. መሣሪያ የያዘ/ች ወይም መሣሪያ ለመያዙ(ዟ) ተጠርጣሪ ሰው መኖሩንና አስቸኳይ እርዳታ እንዲደረግ ወዲያውኑ ለፖሊስ ማሳወቅ፤ ወይም፣

2. ከጦር መሣሪያ/ጠመንጃ፣ ሽጉጥ ወዘተ ሌላ መሳሪያ ይዞ/ዛ የተገኘ/ች ወይም መሳሪያ ስለመያዙ/ዟ ለተጠረጠረ/ች ሰዉ ስለ ተጣሰዉ ህግ በማሳወቅ በሰላማዊ መንገድ ለርእሰ መምህር ወይም ለተወከለ ሰው መሣሪያውን እንዲያስረክብ/እንድታስረክብ እድል መስጠት።

C. ርእሰ መምህር/ተወካይ እንደተማሪዎቹ የዕድሜ ክልል፣ ከሚያስከትሉት አደጋ አንፃር ሁኔታዎችን በማገናዘብ የጦር መሳሪያዎችን ከተማሪዎች የመቀማት/የመውረስ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ አስፈላጊዉን ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸዉ።

D. መሣሪያውን የያዘው ሰው ተማሪ ከሆነ/ከሆነች፣ በተቻለ ፍጥነት ለወላጆች/ለሞግዚቶች በርእሰ መምህር አማካይነት ይነገራቸዋል።

E. ጥይት የሚተኩስ መሣሪያ (ጠመንጃ፣ ሽጉጥ፣ ወዘተ)፣ ተተኳሽ መሣሪያ የሚመሳሰል፣ ወይም ሌላ ዓይነት መሣሪያ በ MCPS ንብረት ክልል ውስጥ ይዞ የተገኘ/ይዛ የተገኘች) ተማሪ በሜሪላንድ ህግ መሠረት የዲስፕሊን እርምጃ ማግኘት ይኖርበታል/ይኖርባታል፤ *MCPS Code of Conduct*፣ MCPS Regulation JGA-RB፣ እገዳ እና ማባረር *(Suspension and Expulsion)*; እና MCPS Regulation JGA-RC, አካለ ስንክልና ያላቸውን ተማሪዎች ማገድ እና ማባረር *(Suspension or Expulsion of Students with Disabilities)*።

F. በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulation COB-RA ድንጋጌ መሠረት ርእሰ መምህር/ተወካይ የተከሰተውን ሁኔታ በተቻለ ፍጥነት ለ OSSI ሪፖርት ያደርጋል/ታደርጋለች፣ አሳሳቢ/አስጊ/ከባድ ክስተቶችን*(ሁኔታ)* ሪፖርት ማድረግ።

ስለ ደንቡ ታሪክ፦ በቀድሞ ስያሜ ደንብ ቁጥር 230-17፣ ኦክቶበር 1/1976፣ የመመሪያ መረጃው የተሻሻለው ጃኑወሪ 1983፣ ኦክቶበር 9/1989 ተሻሻለ፣ ጁን 11/1993 ተሻሻለ፣ ኦክቶበር 4/1996 ተሻሻለ፣ ጁላይ 20/1998 ተሻሻለ፣ ኦክቶበር 13/1999 ተሻሻለ፣ የጽ/ቤቱ ስያሜ ጁን 1/2000 ተሻሻለ፣ ፌብሯሪ 10/2006 ተሻሻለ፣ ኦገስት 11/2014 ተሻሻለ።